እለሂ ተመይጡ ኀበ አምልኮቱ ሕስምት ሦዑ ለአጋንንት እምፍርሀተ ኵነኔ ወእለሂ ተሰዱ ተኀብኡ ውስተ አድባር ወበዐታት ወግበበ ምድር፡፡ ወእለሂ ተርፉ ውሑዳን ውስተ አብያተክርስቲያን አሕሰሙ ሃይማኖተ ኵሉ ነበበ በከመ ፈቀደ ወመሀረ በከመ ሐለየ፡፡

፮ ወእምዝ ተሰምዐ ድምፀ ዕልወቱ ለአርዮስ እንዘ ዓዲሁ ዲያቆን ወይቤ ክርስቶስ ፍጡር ውእቱ ለመድኃኒተ ዓለም ዘተፈጥረ፡፡ ወሶበ ሰምዐ ዘንተ አውገዞ ጴጥሮስ ወሰደዶ አፍአ እምቤተክርስቲያን፡፡ ወሖረ አርዮስ ኀበ አኪላስ ወእለእስክንድሮስ ቀሳውስት ወሰአሎሙ ያስተብቍዕዎ ለጴጥሮስ ሊቀጳጳሳት ከመ ይፍትሖ እምግዘቱ፡፡

፯ ወሖሩ እሙንቱ ቀሳውስት ኀበ ጴጥሮስ ሊቀጳጳሳት ሰገዱ ወአስተብቍዕዎ በእንተ አርዮስ ከመ ይፍትሖ እማእሠረ ግዘቱ፡፡ ወአበዮሙ ጴጥሮስ እንዘ ይብል አርዮስ ፍሉጥ ወሊሉይ እምስብሐተ ኢየሱስ ክርስቶስ፡፡ ወእሙንቱሂ አንሥኡ አስተብቍዖ በእንተ አርዮስ እንዘ ይመስሎሙ ከመ ይትመየጥ ኀበ ርትዕት ሃይማኖት፡፡

፰ ወሶበ አጽሐብዎ ብዙኀ አዘዘ ጴጥሮስ ከመ ይትገኃሡ ሕዝብ ወይትርፉ ምስሌሁ አኪላስ ወእለእስክንድሮስ ወይቤሎሙ አስተርአየኒ በዛቲ ሌሊት እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ በአምሳለ ሕፃን ብሩህ ወይቴጽር ገጾ እምኀዘን ወይለብስ ሥጡጠ አልባሰ ወይእኅዝ ሥጠተ ልብሶ በክልኤ እደዊሁ፡፡ ወእቤሎ አ እግዚእየ መኑ ሠጠጠ ለልብስከ፡፡ ወይቤለኒ አርዮስ ሠጠጠ ለልብስየ ዑቅ ኢትትወከፎ፡ እስመ ሀሎ ጽባሔ ያስተብቍዑከ በእንቲአሁ ዘከፈለኒ እመለኮተ አቡየ ኢይትዌከፎ መለኮተ አቡየ ውስተ መንግሥቱ፡፡ወእምዝ ኀደገ አስተብቍዖቶ ለሊቀ ጳጳሳት እሙንቱ ቀሲሳን፡፡ ወእምድኅረዝ ተፈነዉ ጠርባናሳተ ሜትራይቄይ ዘውእቶሙ ጋላት በትእዛዘ ዲዮግልድያኖስ ከሀዲ ከመ ይምትሩ ርእሶ በእንተ ዘቤዘዎሙ ለዌዋ መርዓንቱ፡፡

፱ ውብፁዕ ጴጥሮስሰ ፈጸመ ስምዐ ዘበሰይፍ ወተከለለ በስመ ኢየሱስ ክርስቶስ ወአንፈሰ እምዝ ዓለም፡፡ ወድኅሬሁ ተሰይመ አኪላስ ወሖረ አርዮስ ወአስተብቍዖ ለአኪላስ ከመ ይፍትሖ እምግዘቱ እንተ ረገሞ ጴጥሮስ፡፡ወፈትሖ እምግዘቱ ወሴሞ ቀሲሰ ወእምዝ ገብአ ኀበ እበዱ ዘትካት፡፡

፲ ወለዲዮግልድያኖስኒ ገፍትኦ እግዚአብሔር እመንበረ መንግሥቱ ወአየሮ በመንክራኵረ ወርቅ ክልኤ አዕይንቲሁ ዘለገሰ ኵለንታሁ ወአጸየ ልሳኑ ወተሰዕረ እመንግሥቱ ወነበረ እንዘ ይስእል ምጽዋተ በአስኳተ አንጾኪያ፡፡ ወነግሠ ህየንቴሁ ቍስጠንጢኖስ ዘእምሥርወ መንግሥተ ሮሜ ዝሕነ ሞገደ ዕልዋን

መከራዎችን አዘዘ፡፡ወደከፋች አምልኮቱ የተመለሱትም ከመከራቸው ፍርሀት የተነሣ ለአጋንንት መሥዋዕት አቀረቡ የተሰደዱትም በተራሮችና በዋሻዎች በፍርኩታዎችም ተሸሸጉ፡፡ በቤተክርስቲያንም የተረፉት ጥቂቶች ሃይማኖትን አጠፉ ሁሉ እንደወደደ ተናገረ እንዳሰበውም አስተማረ፡፡

፮ ከዚህ በኋላ ገና ዲያቆን ሳለ የአርዮስ የክህደት ድምፅ ተሰማ ክርስቶስ ዓለምን ለማዳን የተፈጠረ ፍጡር ነው አለ፡፡ ጴጥሮስም ይህንን በሰማ ጊዜ አውግዞ ከቤተክርስቲያን አስወጣው፡ አርዮስም ቀሳውስት ወደሆኑት ወደ አኪላስና ወደ እለእስክንድሮስ ሄዶ ከውግዘቱ ይፈታው ዘንድ ከሊቀጳጳሳቱ ከጴጥሮስ እንዲያማልዱት ለመናቸው፡፡

፯ እኒያም ቀሳውስት ወደ ሊቀጳጳሳቱ ወደ ጴጥሮስ ዘንድ ሄዱ፡ እጅ ነሡት ከውግዘቱ ማሠሪያም ይፈታው ዘንድ ስለአርዮስ ተማፀኑት ጴጥሮስ ግን አርዮስ ከኢየሱስ ክርስቶስ ክብር ፈጽሞ የተለየ ነው ብሎ እንቢኝ አላቸው፡፡ እነርሱም ወደ ቀናችይቱ ሃይማኖት የሚመለስ መስሏቸው ስለአርዮስ አብዝተው ማለዱት፡፡

፰ አብዝተው ባስጨነቁት ጊዜ ጴጥሮስ ሕዝቡ እንዲርቁ አኪላስና እለእስክንድሮስ ግን ከእርሱ ጋር እንዲቆዩ አደረገ፡ አላቸውም በዚህች ሌሊት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በብሩህ ሕፃን አምሳል ተገለጠልኝ ፊቱን በኀዘን ቋጥሮ ነበር የተቀደደ ልብስ ለብሶ ነበር፡፡ እኔም ጌታዬ ሆይ ልብስህን ማን ቀደደው አልሁት እርሱም አርዮስ ልብሴን ቀደደው ዕወቅ አትቀበለው በነግህ ስለርሱ ይለምኑህ ዘንድ አላቸውና ከአባቴ መለኮት ስለለየኝ የአባቴ መለኮት በመንግሥቱ አይቀበለውም፡፡ከዚህ በኋላ ቀሳውስቱ ሊቀጳጳሳቱን መማፀኑን ተዉት፣ ከዚህም በኋላ የሞርሞንቄን ምርኮኞች ስለታደጋቸው ራሱን ይቆርጡት ዘንድ በከሀዲው በዲዮቅልጥያኖስ ትእዛዝ ጠርባናሳት ሜትራይቄይ የተባሉ ጭፍሮች ተላኩ፡፡

፱ ብፁዕ ጴጥሮስም በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በሰይፍ ተከልሎ ምስክርነቱን ፈጸመ ከዚህም ዓለም አረፈ፡፡ ከእርሱም በኋላ አኪላስ ተሾመ፡፡አርዮስም ሄዶ ጴጥሮስ ካወገዘው ውግዘት ይፈታው ዘንድ አኪላስን ተማፀነው፡፡ እርሱም ከውግዘቱ ፈትቶ ቅስና ሾመው ከዚህም በኋላ ወደ ቀደመ ስንፍናው ተመለሰ፡፡

፲ ዲዮቅልጥያኖስንም እግዚአብሔር ከመንግሥቱ ዙፋን ገለበጠው ሁለት ዓይኖቹንም በወርቅ መንኵራኵር አሳወረው ሁለንተናው ቆስለ አፉም ሸተተ ከመንግሥቱም ተሻረ በአንጾኪያ ጉዳናዎች ምጽዋት እየለመነ ኖረ፡ በርሱም ፈንታ ከሮም መንግሥት ወገን የሆነ ቈስጠንጢኖስ ነገሠ የከሀዲዎች ሞገድ ቆመ የኃጢአትም

